# <u>ከእግዚአብሔር ጋር የጠለቀ ግንኙነት ማድረግ</u>

## ክፍል ፫

### <u>ሰው በእግዚአብሔር አይን ክቡር ነው</u>

ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አምሳል ነው *"እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ"(ዘፍ. 1፡26)።* እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሁሉ ሲፈጥር ይሁን እያለ በቃሉ ነው የፈጠራቸው ሰውን ግን በራሱ አምሳል ነው የፈጠረው። መዝሙረኛው በመዝሙር 8 ላይ እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክ ሲፈጥረው፤ ሰውን ሁሉ በእኩል መልክ እደሚመለከትና የእርሱንም ባህሪ በተለያየ ሁኔታ በፈጠረው ሰው ሁሉ ላይ እንዳስቀመጠ፣ እግዚአብሔርም ለማንም እንደማያዳላ ያሳየናል። በዚህም ላይ ጨምሮ እግዚአብሔር በፈጠራቸው ፍጥረታቶች ሁሉ ላይ ሰውን እንደሾመውና ሁሉንም ከእግሩ በታች እንዲገዙለት እንዳደረገ እንመለከታለን።

"የጣቶችህን ሥራ ሰማዮችን ባየሁ ጊዜ፥ ጨረቃንና ከዋክብትን፣
ታስበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ትጐበኘውም ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው?አንተ የሠራሃቸውን፥
ከመላእክት እጅግ ጥቂት አሳነስኸው በክብርና በምስጋና ዘውድ ከለልኸው።
በእጆችህም ሥራ ሁሉ ላይ ሾምኸው ሁሉን ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት፥
በጎችንም ላሞችንም ሁሉ ደግሞም የምድረ በዳውን እንስሶች፥
የሰማይንም ወፎች የባሕርንም ዓሦች፥ በባሕር መንገድ የሚሄደውንም ሁሉ።"
(መዝ. 8፡3-8)

እኛም በእግዚአብሔር አምሳል እንደተፈጠርንና በእርሱም አይን ክቡር እንደሆንን ልናውቅ፣ ሰው ለሚያምነው ሰው ያለውን ነገር አሳልፎ እንደሚሰጥ እግዚአብሔርም እኛን አምኖ በፍጥረታት ሁሉ ላይ ኃላፊነት እንደሰጠን በመገንዘብ ከእርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት በማድረግ የእለት ተእለት ጉዞአችንን እንድንጓዝ ጌታ ይርዳን።